ደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማ የ 2016 ዓ/ም በጀት ዓመት የድርጅቱ የስራ እንቅስቃሴ ወይም የሒሳብ ስራ በውጭ ኦዲተሮች በጨረታ አወዳድሮ ኦዲት ማስደረግ ይፈልጋል።

የተለቀቀበት ቀን: ሶኒ ጥቅምቲ 4, 2017 (ከ 1 ዓመት)
መዝግያ ቀን: ረቡዕ ጥቅምቲ 13, 2017 04:00 ጥዋት (ተዘጋ)
የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:2%
ቦታ:መቐለ
የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:200.00
ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: ረቡዕ ጥቅምቲ 13, 2017 04:30 ጥዋት
ምድብ: ኣካውንቲን ተዛማድኡን/ ኦዲት ተዛማድኡን/

በድጋሚ የወጣ የኦዲት ጨረታ ማስታወቂያ

ደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም አ/ማ የ 2016 ዓ/ም በጀት ዓመት የድርጅቱ የስራ እንቅስቃሴ ወይም የሒሳብ ስራ በውጭ ኦዲተሮች በጨረታ አወዳድሮ ኦዲት ማስደረግ ይፈልጋል።

የሚከተለው መስፈርት የምታሟሉ የኦዲት ተቋማት /Aud Fims/ እንድትወዳደሩ ድርጅታችን ይጋብዛል።

1. ተጫራች በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መስፈርት መሰረት ከAABE (Accounting and Auditing Board of Ethiopia) ፍቃድ ያለው ሆኖ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርና ቫት ተመዝጋቢ መሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል።

2. ተጫራች የ2016 ዓ/ም የሚገባውን የመንግስት ግብር የከፈለና የ2016 ዓ/ም ንግድ ፍቃድ ያሳደሰ መሆን አለበት።

3. ተጫራች ለጨረታው ማስከበርያ የሚሆን ከጠቅላላ ዋጋ ከ 2% ያላነሰ በባንክ የተረጋገጠ በCPO ብቻ ማስያዝ ይኖርበታል።

4. ተጫራቹ ለኦዲት ስራ በዝርዝር ከቀረቡለት ንኡስ ቅርጫፎች፣ ቅርጫፎችና ዋና መስሪያቤቱ ጨምሮ በኣሰራሩ መሰረት ቢያንስ 50% /አምሳ በመቶ/ ኦዲት የሚደረጉ ሆነው በ2015 ዓ/ም በውጭ ኦዲተሮች ኦዲት ያልተደረጉ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ይሆናሉ።

5. ከታች በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሰረት ብቁ የሰው ሃይል በማዘጋጀት ለስራ የሚሆኑ ሁለት ተሸከርካሪዎች ከድርጅታችን ተመድቦለት ስራው ከተጀመረ በውኃላ በአንድ ወር ተኩል ወይም 45 ተከታታይ ቀናት ስራውን ጨርሶ ለድርጅቱ ማስረከብ የሚችል መሆን አለበት::

6. ተወዳዳሪው በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ መመርያዎች መሰረት በማድረግ ባለፉት ሁለት ተከታታይ ዓመታት በድርጅታችን ውስጥ በኦዲት ስራ ያልተሳተፈ መሆን አለበት።

7. የኦዲት ስራ አስኪያጅ /Audit Manager/ በፋይናንስ ተቋማት በኦዲት ስራዎች ሶስት ዓመትና ከዚያ በላይ የስራ ልምድ ያለው ሆኖ ሁሉም የኦዲት አባላት ሰፊና ውስብስብ ስራ ባላቸው የባንኮችና የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት የሒሳብ ስራዎች ኦዲት በማድረግ በቂ እውቀትና ልምድ ያላቸው መሆናቸው የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው::

8. በኢ/ያ ብሄራዊ ባንክ ህግ መሰረት ሁሉም የኦዲት ቡድን አባላት የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሪፖርቲንግ ስታንዳርድ /FRS/ መሰረት በማድረግ የሰለጠኑበት ሰርቲፊኬት ማቅረብ የሚችሉ፣ ከዚህ በተጨማሪ በ EBS ስራዎች በቂ እውቀትና ልምድ ያላቸው መሆን

ይገባቸዋል።

9. ተጫራች አሁን ባለው ሁኔታ በጥሩ አቋም የሚገኝ በህግ ያልታገደ ወይም ያልተከሰሰ፣ የመፍረስ አደጋ ያልተጋረጠበት መሆን አለበት።

10. በኢ/ያ ብሄራዊ ባንክ መለክያዎች የኦዲት ቡድን አባላት በንብረት ዋጋ አወሳሰንና አተማመን በተመለከተ በቂ ስልጠና የወሰዱ እንዲሁም በእውቀት የተመሰረተ ትክክለኛና ፍትሃዊ ግምት ማስቀመጥ የሚችሉ፣ሰፊና ውስብስብ የማይክሮ ፋይናንስ ስራዎችና የሚጠቀምባቸው አሰራሮች የመገምገምና የመረዳት ችሎታ ያላቸው መሆን ይገባቸዋል፡፤

11. በኢ/ያ ብሄራዊ ባንክ የኦዲት ኣሰራር መሰረት በማድረግ የኦዲት ቡድን አባላት የኦዲት ስራው በትክክለኛ መንፈስና ነፃነት ስራቸው ለማከናወን ሲባል ባለፉት ሶስት ዓመታት የማይክሮ ፋይናንሱ ሰራተኛ ያልነበሩ መሆናቸው ማረጋገጥ ይገባል።

12. በኢ/ያ ብሄራዊ ባንክ የስነ ምግባር መስፈርቶች መሰረት በማድረግ የሚከተሉት አካላት የውጭ ኦዲት አጋር ወይም አባላት አለመሆናቸው በሚቀርብለት ቃለ-ማሃላ ማረጋገጥ የሚችል።

I. ኦዲት ለሚደረገው ተቋም ባለ አክስዮን /Shareholder/፣ ዳይሬክተር ወይም የማይክሮ ፋይናንስ ሰራተኛ አለመሆናቸው፣

II. በፍርድ ቤት ያልተገባ ስራ በመስራት ኪሰራ የታወጀበት አለመሆኑ፣

III. በማንኛውም ወንጀል ወይም የወንጀል ድርጊት ማለት በማጭበርበር ወይም በማታለል፣ በገንዘብ ወንጀል _ ወይም በሌሎች ህገወጥ ተግባራት በመሳተፍ በፍርድ ቤት ያልተፈረደባቸው መሆናቸው፣

IV. በማንኛውም ይክሮ ፋይናንስ ተቋም ወይም በሌላ የገንዘብ ተቋም አባል አለመሆናቸው

V. በማንኛውም የግብር ግዴታ ተጠያቂ አለመሆናቸው ማረጋገጥ የሚችል።

13. በኢ/ያ ብሄራዊ ባንክ የውጭ ኦዲተሮች መርህ መሰረት የውጭ ኦዲተር፣ የስራ አጋሮቹ ወይም የሒሳብ ቡድን አባላት እንዲሁም ተባባሪዎቻቸው ምንም ዓይነት የተቀማጭ ሒሳብ እንዳይሰሩና በክንድ ርዝመት ካልሆነ በስተቀር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተበዳሪ ወይም የማይክሮ ፋይናንስ ተቋም ተጠቃሚ አለመሆናቸው ማረጋገጥ ይገበዋል።

14. በኢ/ያ ብሄራዊ ባንክ መስፈርቶች መሰረት በኦዲት ውል ላይ አንድ የኦዲት ድርጅቱ በባለቤትነት፣ በዳይሬክቶሮችና በስራ አስኪያጆች ላይ በሚኖረው ለውጥ ምክንያት በዚህ መመርያ ላይ የተቀመጠውን መስፈርት ሳይፈፅም ከቀረ እንዲሁም በድርጅቱ ወይም በማናቸውም የሒሳብ ቡድኑ አባላት ላይ የሚወሰድ ማናቸውም ዲስፕሊን ወይም ህጋዊ እርምጃ ውሉ ሊሰረዝ እንደሚችል በግልፅ መታወቅ አለበት::

15. በኢ/ያ ብሄራዊ ባንክ መመርያ በሚያዝዘው መሰረት አንድ የውጭ ኦዲተር ለእያንዳንዱ ቀጠር ወይም ዳግም ቀጠሮ በዚህ መመርያ Annex I እና 1 መሰረት ቀደም ተከተል የፃፈውን የነፃነት ማረጋገጫ እና ተገቢ አዋጅና ፎርም አክብረው ጨርሰው እንዲያቀርቡ ያስፈልጋል።

16. ተጫራቾች የጨረታው ሰነድ ከጥቅምት 04/02/2017 ዓም ጀምሮ ከደደቢት ብድርና ቁጠባ ተቋም ዋና መስሪያቤት መቐለ ቅርጫፍ ቁጥር 2 ከሚገኘው ፅ/ቤታችንና አዲስ አበባ ላይዘን ኦፊስ ቦሌ ዳሞ ሆቴል አከባቢ ከሚገኘው ፅ/ቤታችን ብር 200.00 /ሁለት መቶ ብር ብቻ በመክፈል መውሰድ ይቻላል።

17. የጨረታ ሰጥን ክፍት ሆኖ የሚቆየው ከጥቅምት 04/02/2017 ዓ/ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 13/02/2017 ዓ/ም ከጥዋቱ 4:00 ሆኖ የጨረታ ሳጥን በዚህ ቀን ልክ 4:00 ስዓት ተዘግቶ በ4፡30 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በደደቢት

ብድርና ቁጠባ ተቋም ኣ/ማ በ4ኛው ፎቅ የፋይናንስ ክፍልና በአዲስ በአዲ ላይዘን ኦፊስ ይከፈታል፡፡ ተጫራቾች ወይም ወኪሎቻቸው ባይገኙም ህጋዊነቱ ድረስ ጨረታው የሚከፈት ይሆናል፡፡

18. የጨረታው አሸናፊ የጨረታው ውጤት ከተገለፀ በውኃላ በተከተታይ 7 ቀናት ውስጥ ወደ

19. የጨረታው አሸናፊ የጨረታው ውጤት ከታወቀ በውኃላ ከጠቅላላ ዋጋ 10% un conditional bank guarantee ማስያዝ አለባት፡፡

20.ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታው ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ለበለጠ መረጃ መቐለ ዋና ቢሮ ሞባይል ቁጥር +251963095665

አዲስ አበባ ላይዘን ኦፊስ +251928277756 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle